# ኖህተ ድል ለኢትዮጵያ

ሰነ ዲሞክራሲን ሁሉ ሰው ይመኛል
ካልታገሉ በቀር ከወዴት ይገኛል።
ብቻዬን ታግዬ ቢያቅተኝ ተውኩት
መተባበርን ነው የተመኘሁት።
ተባብሮ መታገል አቃተን ያላችሁ
ድሉ በነጠላ አይገኝላችሁ።
ህብረት ይበል ቅንጅት አንድነት ይበል ወይ ሌላ
ከስሙ ምን አላችሁ
ትልቁ ነገር ትብብራችሁ
ወያኔን ለመጣላችሁ
ቁሳቁስ ገንዘብ አይቸግራችሁ
እስከ መቼ ነው ወሬአችሁ
ባንድ ብትነሱ ታሸንፉላችሁ።
ህብረቱም ትግል ይጠይቃል ወይ
መሆኑ ቀረና የህዝቡ ዋይ ዋይ።
እረ የናንተስ ከማንም አይገጥም
እንኳን ላየነው ለሰሚው አይጥም።
ወያኔ ፍራቻው አንድነት
ትልቁ ጦሩ ኅጥነት
የናንተ ይብስ መከተሉ
ተባበሩ እንጂ ችላ አትበሉ
ለድል እንዲያበቃን ትግሉ።
ከነጠላ እና ከህብረት
ማን ይበልጥ ይሆን ቢሰፍሩት
ለኔ ህብረቱ ይበጀኛል
ለነጻነቴ ያበቃኛል።
ሌላ ምን ይገኛል ከዚህ ወዲያ
ኖህተ ድል ነው ለኢዮጵያ።

**ክንፈ ሚካኤል**
**ሜልበርን**
**፳፻፩ ዓ/ም**